# ቀስተደመና ሬድዮ ትችት

(ከመላ ኢትዮጵያ ሶሻሊስት ንቅናቄ ስነጽሁፍ ዝግት ክፍል የቀረበ)

(ግንቦት 23 ቀን 1994 ኢ.ም.)

# ለምን ቁንጽል ውንጀላ?

መለስ ዜናዊ በአለፈው ሳምንት «ኔፓድ» ተብሎ በሚታወቀው አዲስ ላፍሪካ ተበጀ በተባለ
ው የልማት ፕላን ስብሰባ ላይ ተገኝተው ባደረጉት ንግግር የምእራብ አገሮች ድሆች አገሮችን «
ባንድ በኩል ገበያችሁን ክፈቱልን በነጻ ገበያ መርህዎች መሰረት ሸቀጣችንን እንደልብ እናፍስስ እ
ያሉ እየጮሁ በሌላ በኩል ደግሞ ድሃ አገሮች በአለም ገበያ ሊወዳደሩባቸው በሚችሉዋቸው የእ
ርሻ ውጤቶች ንግድ ላይ ለገበሬዎቻቸው በቢልዮን የሚቆጠር ዶላር ድጎማ በማድረግ ተወዳድረን
ምርቶቻችንን እንዳንሸጥ እያደናቀፉን ነው» በማለት በማማረር ወንጅለዋል። በስፍራው የተገኘው
አንዳንድ የአፍሪካ አገሮች መሪዎችንም ያካተተ ተሰብሳቢ በዚህ ንግግራቸው ተደስቶ ብድግ ብሎ
በማጨብጨብ ድጋፉን ገልጾላቸዋል። የአለም መገናኛ ብዙሃንም «መለስ ዜናዊ ምእራብ አገሮችን
ልክ ልካቸውን ነገሩዋቸው» በሚል መንፈስ ይህንን ትልቅ ዜና አድርገው ሲያናፍሱ ከርመዋል።

እኛ ግን አናጨበጭብም። ይህንን የመለስን አቋዋም እንደትልቅ ነገር አርገንም አናናፍሰው
ም። አንደኛ ተብሎ ተብሎ ያለቀለት ውንጀላ እንጂ ምንም አዲስ ነገር የለውም።ሁለተኛ ይህ ው
ንጀላ እጅግ በቁንጽሉ የቀረበ በመሆኑ የበለጸጉት አገሮች ፖሊሲ በኛም ሆነ በሌሎች እየደኸዩ በ
መሄድ ላይ ባሉ አገሮች እያደረሰ ስላለው ውድመት ፍንጭ እንኳዋን አይሰጥም። ሶስተኛ ይህ የ
ድጎማና በአጠቃላይ የበለጸጉት አገሮች በአለም ንግድ የሚከተሉት ፖሊሲ ከነዚህ አገሮች የኢኮኖ
ሚ ጥቅምና ከፖለቲካ መሪዎቻቸው የስልጣን የዞታ ጋር በጥብቅ የተቆራኘ በመሆኑ በድሃ አገሮች
መሪዎች ዲስኩርና መማጸን ይቀየራል ማለት ዘበት ነው። አራተኛ እነአቶ መለስም ሆኑ ሌሎች የ
አፍሪካ መሪዎች በዚህ መልክ ምእራባውያንን «እዙሩልን አሰራራችሁን ቀይሩ» እያሉ የሚሰነዝሩት
«የማይመስል» መማጸን ፍሬ ይሰጣል ብሎ መገመት ራስን ማታለል ብቻ አይደለም። መቀየር ያለ
በት የምእራባውያን አሰራር ሳይሆን የአፍሪካ አገሮች የልማት አቅጣጫና ስትራቴጂ እንደሆነ የማ
ይገነዘብ አጉል አካሄድ ነው።

አንደኛ ይህ ውንጀላ ተብሎ ተብሎ ያለቀለት ውንጀላ እንጂ አዲስ ነገር የለውም።

አቶ መለስ ያማረሩበት የእርሻ ድጎማ ጉዳይ ለብዙ አመታት የደቡብ አገሮችን ብቻ ሳይሆ
ን የበለጸጉትንም አገሮች ሲያተራምስ የቆየ ጉዳይ ነው። የዩናይትድ ስቴትስ፣ የአውሮፓ ህብረትና
ሌሎች መንግስታት በዚህ መልክ እስከዛሬ ለገበሬዎቻቸው የሚያደርጉት ድጎማ በቀን አንድ ቢልዮ
ን ዶላር መሆኑ በየጊዜው የሚተችበትና በተለይም ካሪን ግሩፕ በተባለው እንደብራዚል፣ አውስትራ
ልያ፣ ደቡብ አፍሪካ፣ አርጀንቲና ወዘተ የመሰሉ የ«አራሽ አገሮች» ስብስብ ሲወገዝ የቆየ አሰራር
ነው። ሰሞኑን ብዙ እየተወገዘ ያለው አሜሪካ ለገበሬዎቿ ያደረገችው የመቶ ዘጠና ቢልየን ዶላር
ድጎማ አዲስ ክስተት አይደለም።

እንደኛ መናጢ ድሃ ሊባሉ የማይችሉት የካሪን ግሩፕ አገሮች ይህንን ብቻ ሳይሆን በአውሮ
ፓ ህብረትም የሚደረገውን ድጎማ «በአለም አቀፍ ደረጃ የነጻ ገበያን አሰራር ያዛባል። ይህ ድጎማ
እያለ ፍትሃዊ በሆነ ዘዴ መነገድና መበልጸግ አልቻልንም» በማለት ይቃወሙታል። ከዚህም አልፈ
ው ይህ ድጎማ የሚሉ ነገር «ድሃ አገሮች» የሚባሉትን የባሰውን ያደኸያል እያሉ ለኛም ይከራከራ
ሉ። በዚህ በፕሬዜዳንት ቡሽ የተጨማሪ ድጎማ ፖሊሲ የኛን አገሮች ገበሬዎች የሚጎዳው እንዴት
ነው? ሌላው ቀርቶ ታይም ማጋዚን በያዝነው ሳምንት የሚለውን እንይ

« አዲሱ ድጎማ በመላው አለም የእርሻ ውጤቶች ዋጋ እንዲሸቀለቀል ያደርጋል።በመልማ
ት ላይ ባሉ አገሮች ገበያ ከውጭ የሚገባው አገር ውስጥ ከሚመረተው ይልቅ ይረክሳል። ይህ ደ
ግሞ ብዙ ገበሬዎችን ከእርሻው አለም እንዲወጡ ያስገድዳቸዋል።» በማለት የሁኔታውን አሳሳቢነ
ት በትክክል ጠቁሙዋል።

ሁለተኛ፣ የአቶ መለስ ውንጀላ ቁንጽል ከመሆኑ የተነሳ ድጎማ እያደረሰብን ያለውን ውድመት ጨርሶ አያንጸባርቅም።

የበለጸጉት አገሮች የይበልጥ ልማትና የብልጽግና ጎዳናን ዘጋብን ብለው የሚቃወሙትን ይህን ፖሊሲ እኛ «በመደህየት ላይ» ያለነው አገሮች የምንቃወመው እስከዚህም «ለብልጽግናችን» ብለን አይደለም። «ለህልውናችን» ብለን ነው። የመለስ ቁንጽል አባባል ጥያቄው ለኛና ለህዝባችን የሞት ሽረት ጥያቄ እየሆነ መምጣቱን አያመለክትም። በመሆኑም ውንጀላቸው ምእራባውያንንም አላስቆጣም። በኛ በኩልም አቶ መለስን የብሄራዊና ፍትሃዊ ኢኮኖሚ ግንባታ ተቆርቋሪ መሪ አያደርጋቸውም። ጉዳዩ ለኛ ገበሬዎች የሞት ሽረት ጥያቄ ሆኑዋል የምንለው ለምንድን ነው? ሁሉም የሚያውቃቸውን ሁለት ዋና ዋና አጥፊ ገጽታዎቹን እንመልከት

አንደኛ በአፍሪካም ሆነ በሌሎች የደቡብ አገሮች እንደሚታየው ከበለጸጉት አገሮች በድጎማ እየታገዘ በኛ አገሮች ገበያዎች የሚፈሰው እህል የኛን ገበሬዎች ያመረቱትን በየሃገሮቻቸው የውስጥ ገበያ የልፋታቸውን መልሰው በሚያገኙበት ተመጣጣኝ ዋጋ ለመሸጥ የማይችሉበት አደገኛ ደረጃ ላይ አድርሷቸዋል። ከዚህም አልፈው ተርፈው ገበሬዎቻችን በዋጋ ማሽቆልቆል የተነሳ ለማዳበሪያ የተበደሩትን መልሶ ለመክፈል ስለማይችሉ ህልውናቸውን የሚፈታተን እዳ ውስጥ እየተዘፈቁ ናቸው። የሃብታም አገሮች ገበሬዎች መንግስቶቻቸው በሚሰጧቸው ድጎማዎች ማካካስ ባይችሉ ኖሮ እኛ አገር እህል «ጥንቡን በጣለ» ዋጋ መሸጥ አይችሉም ነበር።

ሁለተኛ በተለይ እንደ ኢትዮጵያ በየጊዜው በርሃብ ለሚጠቁ አገሮች እርዳታ እየተባለ የሚገባው እህል ጉዳይ አለ። እርዳታው የሚሰጠው እነዚህ አገሮች የርሃብን ችግር ለማስወገድና አንድ ቀን ራሳቸውን ለመቻል በሚያበቃቸው መልክ እንዳይደለ እኛም አቶ መለስም አሳምረን እናውቀዋለን። ጉዳዩ ከአለፉት ሃያና ሰላሳ አመታት ጀምሮ እስካሁን እያወዛገበ ያለ ጉዳይ ነውና።

አንድ አገር ተራበ ሲባል በዚያ አገር ያለው ህዝብ በሙሉ አላመረተም፣ አንድ አገር ድርቅ መታው ሲባል በዚያ አገር በሁሉም አካባቢዎች አውዳሚ ድርቅ ገብቷል ማለት አይደለም። ደግሞ ተደጋግሞ እንደታየው ባንድ ለርሃብ በተጋለጠ አካባቢ ለሚኖር ህዝብ የሚበቃ ምግብ በዚያው አገር በሌላ አካባቢ ይገኛል። ከዚህ ሃቅ በመነሳት ለህዝቦች መብት ተሟጋች የሆኑ ወገኖች « እንርዳ» ከተባለ ለርሃብ የሚቀርበው እርዳታ በገንዘብ መልክ ሆኖ የእርዳታው እህል በዚያው አገር ውስጥ ካሉ ትርፍ አምራች ገበሬዎች ይገዛ እያሉ ይሟገታሉ። እርዳታው በዚህ መልክ ሳይሆን በእህልና በሌላ የፍጆታ እቃ መልክ ከሆነ ግን እርግጥ ባጭር ጊዜ ሲታይ ነፍስ ሊተርፍ ይችላል በረጅም ጊዜ ሲታይ ግን የተራበውንም መልሶ ሳያቋቁም በሃገሪቱ ትርፍ አምራቹንም ገበሬ ገበያ በመንፈግ ቀስ በቀስ ገደል ይዞ ሊገባ የሚችል አሰራር ነውእያሉ ያስጠነቅቃሉ።

በያዝነው አመት በሃገራችን በአጠቃላይ የእህል ዋጋ የድሃውን ገበሬ ህልውና አደጋ ላይ በሚጥል ሁኔታ ተሽቆልቁሎ ድሃው ገበሬ እጅግ አስቸጋሪ ሁኔታ ውስጥ ገብቷል። የዚህ ምክንያት ምንድን ነው? በያዝነው ሳምንት የተባበሩት መንግስታት ድርጅት ጉዳዩን አስመልክቶ ባወጣው አንድ ሪፖርት ላይ ለዚህ ተጠያቂ የሚሆኑት በድጎማ ታግዘው በአልባሌ ዋጋ ገበያ ላይ የሚፈሱት የውጭ አገሮች የእርሻ ውጤቶችና በእርዳታ ስም ወደ ኢትዮጵያ የሚገባው እህል እንደሆኑ በግልጽ ሲያመለክት

« ከ1992 አ.ም. ጀምሮ በኢትዮጵያ አስጊ የሆነ የሰብል ዋጋ መሽቆልቀቆል ይታያል። ይህ የሆነው ትርፍ ከሚያመርቱ አካባቢዎች በተገኘው ምርት፣ ከውጭ እየመጣ ለገበያ በሚቀርበውና በእርዳታ ስም ወደ ሃገሪቱ በሚገባው እህል ምክንያት ነው» በማለት ምክንያቶቹን ዘርዝሮ ይህ ችግር በሚልዮን የሚቆጠሩ ገበሬዎችን ህይወት እንዴት በማናጋት ላይ እንደሆነና ብዙ ገበሬዎች ካለፉት አመታት ዛሬ ለምን ይበልጥ ድሃ እንደሆኑ ያብራራል። (ኢሪን 04/06.2000)

ሶስተኛ አቶ መለስ የሚወነጅሉት የሃብታም አገሮች አሰራር በድሃ አገሮች መሪዎች ዲስኩርና መማጸን አይቀየርም።

ይህ አሰራር የኛን አገሮች ገበሬዎች ህልውና የሚፈታተነውን ያህል ከበለጸጉት አገሮች የኢኮኖሚ ጥቅምና ከመንግስታት የፖለቲካ ይዞታ ጋር በጥብቅ የተቆራኘ አሰራር ነው።

ይህ እርዳታ በዚህ አይነት አጥፊ መልክ የመቅረቡ ጉዳይ ከሶስት ወራት በፊት ሜክሲኮ አገር ሞንቴሮ በሚባለው ከተማ ድሆች አገሮችን ካሉበት ችግር ለማውጣት ምን አይነት ርዳታ እን

ደሚያስፈልግ ለመወያየት በተደረገው የአለም መሪዎች ስብሳባ ላይ ብዙ አወዛግቧል። በዚህ ስብሰ ባ ላይ ከአሜሪካ መንግስት ለየት ያለ አቋም ይዞ የነበረው የአውሮፓ ህብረት *«ርዳታ በገንዘብ ይ ሁን ምግብ ከዚያው ከሃገሩ ገበሬ ይገዛ»* የሚለውን ሃሳብ ለማስተናገድ የሚያስችል የፖሊሲ ለው ጥ እያሰበ መሆኑ ይታወቃል። የአሜሪካን መንግስት አቋም ግን «እርዳታ በጥሬ ገንዘብ» የሚለውን ፖሊሲ ይቃወማል።

ባለፈው ወር አገራችን ለጉብኝት መጥተው የነበሩት የአሜሪካን ኮንግረስ አባል የሆኑት ሚስ ተር ጂም ኮልበ በምንም በማያሻማ ሁኔታ የመንግስታቸውን አቋም አስረግጠው ተናግረዋል። ኢሪን የተባለው የተመድ የዜና አውታር በጉዳዩ ሲያትት «አሜሪካ እርዳታን ከዚያው ከሃገሩ ገዝቶ ማቅ ረብ የሚለውን አሰራር በመቃወም አወዛጋቢ የሆነውን አሰራሯን ልትቀጥል ነው» ካለ በኋላ የኮንግ ረስ አባሉን በመጥቀስ

« ገንዘቡንም እህሉንም የምንሰጠው እኛ እንደመሆናችን መጠን የመጀመሪያው ግዴታችን እህሉን ከዩናይትድ ስቴትስ መግዛትና ከዚያም በዚህ የምግብ እርዳታ ፕሮግራም ተጠቃሚ ወደሆነ ው አገር መላክ ነው።» በማለት እቅጩን መናገራቸውን ዘግቧል።

አቶ መለስ ባስጨበጨቡበት ንግግራቸው ላይ ባወገዙት የእርሻ ድጎማም ጉዳይ ቢሆን ከበለ ጸጉት አገሮች በኩል የሚለወጥ ነገር እንደማይኖር ለመረዳት ይህንን አወዛጋቢ የመቶ ዘጠና ቢልዮ ን ዶላር ህግ ሲፈርሙ ፕሬዜዳንት ቡሽ ያሰሙትን ቃል መመልከት ብቻ ይበቃል።

ፕሬዜዳንቱ በዚህ ንግግራቸው ይህ የድጎማ እርምጃ አስፈላጊ ሆኖ የተገኘው የአሜሪካን ገበ ሬዎች የኑሮ ሁኔታ (ወይ አፍ ላይፍ) ከትውልድ ትውልድ ተረጋግጦ እንዲቀጥል ለማድረግ ነው ካ ሉ በኋላ በዚህ የእርሻ ንግድ ጉዳይ በመከተል ላይ ያሉትን ፖሊሲ ምንነት ሲያብራሩ « በመላው አለም ምግብ ለሚያስፈልጋቸው ህዝቦች ሁሉ ስጋም እህልም ለመሸጥ እንፈልጋለን። መንግስቴ ገበ ያ ለማስፋፋት ሳያሰልስ በመስራት ላይ ያለ መንግስት ነው።» በማለት ቢያንስ በአጭር ጊዜ ለውጥ ሊጠበቅ እንደማይቻል አመልክተዋል።

ይህ እንግዲህ ወደ መጨረሻውና አራተኛው ነጥብ ያመጣናል። የአሜሪካንም መንግስትንም ሆነ ሌሎች የበለጸጉት አገር መንግስታትን ለምን የሃገራችሁንና የህዝባችሁን ጥቅም አስቀድማችሁ እኛን ታደናቅፋላችሁ ብሎ መወንጀልና አቋም ቀይሩ ብሎ መማጸን አጉል መመጻደቅ ነው። መለ ወጥ ያለበት የነሱ ሳይሆን የኛ የድሃ አገሮች የልማት ስትራቴጂና አቅጣጫ ነው። አቶ መለስ ይህ ንን ቁንጽል ውንጀላቸውን የሰነዘሩበት ስብሰባ እንዲያውም አፍሪካን «አዲስ» የልማት አቅጣጫና ስትራቴጂ ጎዳና ያስይዛል ተብሎ በተነደፈው ኔፓድ (ወይም ኒው ፓርትነርሽፕ ፎር አፍሪካን ዲቨ ሎፕሜንት) በተባለው ሰነድ ላይ ለመወያየት የተጠራ ስብሰባ ነበር። ችግሩ ይህ አዲስና ከዚያም አልፎ ተርፎ «አፍሪካዊ በቀል» ተብሎ ብዙ የሚለፈፍለት እቅድ ምንም አዲስ ነገር የለውም። የ አፍሪካዊነትም ነገር ከተነሳ ከአፍሪካ ህዝቦች ጥቅምና ብልጽግና ጉጉት የሚነሳ ሳይሆን ከአለም አ ቀፍ የፋይናንስ ተቋዋሞች ጋር በመመሳጠር የተነደፈ ስትራቴጂ በመሆኑ በብዙ አፍሪካዊ ምሁራን ና ድርጅቶች አካባቢ ተቃውሞ እያጋጠመው እናያለን። ይህንን በቀጣይ እትም በሰፊው ለማብራራ ት እንሞክራለን።